እነ እሰየና ተወልደ ያሻቸውን ያህል ከመለሰና በረከት ጋር   በከረረ ጸብ ላይ የሰነበቱ ቢሆኑም ተቁዋሚዎች ዘለው ቤተ መንግስት እንደሚገቡባቸው ስለሚያውቁ ሥልጣን ወደ እነሱ እንደሚገባ ካላረጋገጡ መለሰን ከስልጣኑ ሊነኩት አይሹም

******************************************

አንድ ኢንጂኔር ዕግዚቢሽን ማዕከል ሊገቡ በሩ ላይ ያለውን ታጋይ ልግባ ይሉታል - በዚህ ሳይሆን መግቢያው በጀርባ ነው ይላቸዋል በዛ ከምዞር በዚ ልግባ ምን ችግር አለ ይሉታል አይቻልም በዛ ግባ ይላቸዋል ኢንጂነሩ እጃቸውን እንደማወናጨፍ ብለው ይመለሳሉ ታጋዩ ጠመንጃውን ያነሳና ይገድላቸዋል ገዳዩ በሚዲያ አልወጣም አልታሰረምም

******************************************

አማሮችን ከሐረር ለማስወጣት በተካሄደው ሤራ - አቶ ደጀኔ  በቀለ የተባሉ ባለ ሆቴል ያልሞተን ሰው ገደሉ ተብለው በደረሰባቸው ድብደባ የአካል ጉዳትና ንብረታቸውን እንዲያጡ ተደረጉ - ሞተ የተባለው ሰው እንዳልሞተ ሲጋለጥ  የእርማት እርምጃ አልተወሰደም

******************************************

የወያኔ ካድሬ አታክልቴ በብዕር ሥም ወያን ፣ “ አቶ ተስፋዬ ገብረአብ እንግሊዘኛ ስለማይችል ፈረንጅ ሲያይ ይሸሽ ነበር” ላለው
አቶ ተስፋዬ ፣ “የደብረዘይት ልጆች ይሄን ሲሰሙ ይስቁበታል ምክንያቱም እኛን High School ያስተማሩን ፈረንጆች ናቸው ደብረዘይት ረሺያን ሕንድ ነበሩ ነበሩ አስተማሪዎቻችን።አታክልቴ ያደገበት ከተማ፣ አጋሜ አካባቢ ነጭ ቁራ ነጭ ወፍ እንኩዋን የለም - ችግሩ የእንገሊዘኛ አልነበረም  ስለ አንድ ትልቅ መስሪያ ቤት በባጀት ጉዳይ ላይና በመዋቅር ላይ እንዴት አድርጌ ነው ንግግር የማደርገው
 በዛ ወቅት  ምንም የማላውቅ  የ 22 ዓምት ወጣት ነበርኩ፤ ስለ ባጀት እና ስለ ድርጅት በእንግሊዘኛ ቀርቶ በአማርኛም አልችልም ነበር፡፤ አሁንም በአርባ ዓመቴም አልችልም ይልቁንም ወያኔ ምንም የማያውቁ በጎሳ ብቻ የተሰበሰበሰቡ ሰዎችን መድቦ  አገሪቱዋን  በየትም አገር ተድርጎ በማይታይበት አኩዋህን እያወደም ነው”።

******************************************

አቶ ያሬድ ጥበቡ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አዲሱ ለገሰን “ ዕውን ብትሸነፉ ሥልጣን ለመልቀቅ ዝግጁ ናችሁ?” ብለው ለጠየቁት ጥያቄ አዲሱ ለገሰ “ሊሆን በማይችል ነገር መልስ አልሰጥህም” የሚል መልስ ሰጥቶዋል።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com